# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች



# ሐብታሙና ድሀው ሰው


ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: Alastair Paterson; M. Maillot; Lazarus
ያሻሸለው (አሻሸሎ የጻፈው): M. Maillot; Sarah S.
የተተረጎመው: Abel Eshetu



አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

BFC
PO Box 3
Winnipeg, MB R3C 2G1
Canada



©2020 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።




ብዙዎቹ የሐይማኖት መሪዎች ከእግዚአብሔር ይልቅ ገንዘብን እንደሚወዱ ኢየሱስ ያውቅ ነበር። ሐብት ያለ እግዚአብሔር ዋጋ ቢስ እንደሆነ ይነግራቸው ነበር። የሁለት ሰዎችንም ታሪክ ነገራቸው። ሐብት የዘላለምን ሕይወት ሊገዛ አይችልም።




በውድ ዋጋ የተገዙ በርካታ ልብሶች የነበሩት አንድ ሐብታም ሰው ነበር።
3
ሐብታሙ ሰው ውድ ውድ ምግብ ይመገብ ነበር። በርካታ አይነት ምግብ ይቀርብለታል። ቁርስ፣ ምሳና እራቱ እጅግ ያማረ ምግብ ነበር። ገንዘቡን ምርጥ ለሆነ ምግብ ያውለው ነበር።
4
በሐብታሙ ሰውዬ ደጃፍ ላይ ግን አንድ በጣም ድሀ የሆነ የተራበና የሚለምን ነው ተኝቶ ነበር። ስሙ አልዓዛር ይባላል።
5
ድሀው አልዓዛር ቁስል ነበረበት። በሽታ ሳይዘው አልቀረም። ክፉ ሰዎች አቁስለውት ይሆናል። ወይንም ድሀ በመሆኑ የተመጣጠነ ምግብ ስለማያገኝ ሰውነቱ ቆስሎ ሊሆን ይችላል።
6
አልዓዛር ምግብ ይፈልጋል። የሀብታሙ ሰውዬን ትርፍራፊ ምግብ ለመብላት የሚፈልግ ይመስላል።
7
በርካታ የመንደር ውሾች ምግብ ሊለቃቅሙ በአጠገቡ ይመጡ ነበር። ውሾቹም ቊስሎቹን ይልሱ ነበር። ማንም ስለአልዓዛር ግድየለውም ነበር።
8

አንድ ጠዋት
ግን አልዓዛር
ከእንቅልፉ
አልነቃም
ነበር። ድሀው፣
ወዳጅ የሌለው
እና የተራበው
አልዓዛር ሞቶ
ነበር።



9

አልዓዛር እንደሞተ ወዲያው ታላቅ
ደስታ ሆነለት። መላእክትም ወደ አብርሃም
እቅፍ ወሰዱት ብሎ ኢየሱስ ተናገረ።
እግዚአብሔር አልዓዛርን አጽናናው።



10

ሐብታሙ ሰውም ሞተ። ሐብትና ገንዘቡ ሊያድነው
አልቻለም። ሞትን ሊከለክልለት የሚችል አልነበረም።



11

ሐብታሙ ሰው ተቀበረ። ምናልባትም ትልቅ ስነስርዓት ተደርጎለት
ይሆናል። ሰዎች ሐብቱንና ስኬቱን በማድነቅ አውርተው ይሆናል።
ግን ይህ ሁሉ ምንም አልጠቀመውም። ነፍሱ ወደ ሲኦል
ገብታለች።



12

እርሱም እየጮኸ፡- አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ፥ በዚህ ነበልባል
እሰቃያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ
አልዓዛርን ስደድልኝ አለ።



13

አብርሃም ግን፡- ልጄ ሆይ፥ አንተ
በሕይወትህ ሳለህ ሁሉ ነገር ነበረህ
አልዓዛር ግን ምንም አልነበረውም።
ሕይወቱ የከፋ ነበር፤ አሁን ግን እርሱ
በዚህ ይጽናናል አንተም ትሰቃያለህ።
ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ
እንዳይችሉ፥ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ
እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ
መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል አለ።



14

አምስት ወንድሞች አሉኝ፤ አልዓዛርን ላከውና ወደዚህ ስቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመስክርላቸው አለ።



15

አብርሃም ግን፦ መጽሐፍ ቅዱስ አለላቸው፤ እርሱን ይስሙ አለው። መጽሐፍ ቅዱስን የማያምኑ ከሆነ፥ ከሙታንም እንኳ አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው።



16

ኢየሱስም የሐብታሙንና ድሀውን ታሪክ በጨረሰ ጊዜ የሐይማኖት መሪዎቹ ራሳቸውን እንዲህ ብለው ሳይጠይቁ አይቀርም። *“ከእግዚአብሔር ይልቅ ሐብትን እወዳለሁ?”* የእግዚአብሔርን ቃል የማያምኑ ከሆነ ምን ሊገጥማቸው እንደሚችል አውቀዋል።



17

ሐብታሙና ድሀው ሰው

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ሉቃስ ወንጌል ምዕ. 16

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

18




19

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝነት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16

20